የሰ/መ/ቁ. 46574

መጋቢት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

**አመልካች ፡-** ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ - ይሁንልኝ ቡሎ ቀረበ

**ተጠሪዎች ፡-** 1. ዮናስ ካሣ አልቀረበም

2. ወ/ሮ በለጡ አጎታለም ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ ሰበር መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለትምህርት (ለስልጠና) የተደረገው ወጪ በውሉ መሠረት ይመለስልኝ በማለት አመልካች የመሠረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው 1ኛ ተጠሪ በውሃ (ወተር) ኢንጂነሪንግ የማስትሬት ዲግሪ ትምህርቱን በአመልካች ድጋፍ እና ትብብር ፈቃድ ወደ ቤልጂየም ሀገር ሄዶ እንዲማር እና ተምሮ ሲመለስም ለተማረበት ሁለት ዓመት ሦስት እጥፍ ማለትም ስድስት ዓመት አመልካችን ለማገልገል፣ ይህን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ ለትምህርት የወጣውን እና ለቤተሰቡ የተከፈለውን ደመወዝ በጠቅላላው ብር 190,470.00 ለአመልካች እንዲከፍል ስምምነት ተደርጎአል፡፡ 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ ግዴታውን ባይወጣ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ገንዘቡን ለመክፈል ግዴታ ገብታለች፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ተመልሶ ለማገልገል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህም ሁለቱም ተጠሪዎች ገንዘቡን ይከፍሉ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ክሱን የመሠረተው፡፡ ክሱ የቀረበለት የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ካየ በኋላ፣ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ ጊዜ በመማር ላይ እንደሆነ ማስረጃ ቀርቦልኛል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ትዕዛዝ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኝ ወገኖች የተገባውን ውል መሠረት ያደረገ

ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጭብጡን ግራቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ለክሱ መነሻ የሆነው ውል በግራቀኙ መካከል ስለመደረጉ እና 1ኛ ተጠሪም ወደቤልጅየም ሃገር ሄዶ የማስተርስ ዲግሪውን ስለማግኘቱ አልተካደም ወይም አከራካሪ አልሆነም፡፡ ተጠሪዎች ክሱን የተቃወሙት 1ኛ ተጠሪ የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ወደ አሜሪካን ሃገር በመሄድ ለፒ.ኤች. ዲግሪ ትምህርት በመቀጠል ላይ ስለሆነ በውሉ መሠረት ተመልሶ አመልካችን ሊያገለግል አልቻለም በሚል ገንዘቡን እንዲከፍል አይገደድም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን በተጠሪዎች የቀረበውን የመከራከሪያ ነጥብ እንዳለ በመቀበል ነው ክሱን ውድቅ ያደረጉት፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የቀጠለውን ትምህርት ጨርሶ ሲመለስ ክሱን ማንቀሳቀስ ይችላል በማለትም ነው ክሱን የሰረዙት፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ የተሰጠውን ውሳኔ የተቃወመው በመሃከላችን የተደረገውን ውል እና ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው እና እንደምንገነዘበው ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በግራቀኝ ወገኖች የተደረገውን ውል እና አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉ በፊት የውሉን ይዘት እንደዚሁም ውሉ ለተዋዋይ ወገኖች የሰጠውን መብት እና የጣለውን ግዴታ መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በክርክሩ እንደተገለጸው አመልካች 1ኛ ተጠሪን በማስተርስ ዲግሪ ለማስተማር ግዴታ የገባ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ደግሞ በውሉ ለተመለከቱት ዓመታት አመልካችን ለማገልገል፤ ይህ ካልተፈጸመ ደግሞ ለትምህርቱ የወጣውን ወጪ ለአመልካች ለመተካት ግዴታ ገብተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በውሉ መሠረት ትምህርቱን ጨርሶ የማስተርስ ዲግሪውን ያገኘ ቢሆንም፤ ወደ አገሩ በመመለስ ለአመልካች አገልግሎት አልሰጠም ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ይህም ማለት ውሉ በሰጠው መብት የተጠቀመ (ትምህርቱን የተማረ) ሲሆን፣ ግዴታውን ግን አልፈጸመም፡፡ የፒ.ኤች ዲግሪ ትምህርት እንዲቀጥል የሚያስችለው ተጨማሪ ስምምነትም ከአመልካች አላገኘም፡፡

በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ስለመሆናቸው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731 በተቀመጠው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ ወይም ከዚሁ በመውጣት በፍ/ቤት ሊተረጎሙ እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1733 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መሠረት የሆነው ውል ግልጽ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ተመልሶ አመልካችን ለማገልገል ግዴታ የገባው የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ትምህርቱን ጨርሶ ዲግሪውን እንዳገኘ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም የማገልገል ግዴታውን መወጣት የሚችለው በኋላ የጀመረውን የፒ.ኤችዲ ድግሪ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ነው ለማለት የሚቻልበት የውልም ሆነ የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ወደሌላኛው ጫፍ (ትምህርቱን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ ክሱ ይቀጥል ወደሚለው) የሄዱት ግልጽ የሆነውን ውል ግልጽ ሆኖ ከሚታየው በመውጣት እንደሆነ ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 03288 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 64401 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በጉዳዩ ሥረ ነገር ገብቶ አመልካች ባቀረበው የክፍያ መጠን ላይ ክርክር እንዲሰማ፣ በመጨረሻም ተገቢውን ይወስን ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.341(1) መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ